# የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች መመሪያ

የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች በግሉ ሴክተር መሰጠታቸው የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመላ ሀገሪቱ እንዲስፋፋ እገዛ የሚያደርግ በመሆኑ ፣

በተለይም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የብሮድባንድ አገልግሎትን መስጠት የሚያስችሉ ኔትወርክ የዘረጋ በመሆኑና ይህንንም አቅም በተሟላ ሁኔታ መጠቀም ይቻል ዘንድ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሕብረት ሥራ ማህበራትን፣ የግሉን ሴክተር እና ሌሎችን ማሳተፍ ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀፅ አንድ
## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች መመሪያ ቁጥር 2/1997» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ ሁለት
## ትርጓሜ

በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991 የተመለከቱት ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈፃሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. «ኤጀንሲ» ማለት የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ ነው፡፡
2. «የኮል ሴንተር አገልግሎት» ማለት አንድ ሰው ራሱ ወይም ሌላ ሰው እየሰራ ስላለው ሥራ ወይም እየሰጠ ስላለው አገልግሎት ወይም ተመሳሳይ ሁኔታን የሚገልፅ ለደንበኛ ወይም ደንበኛ ለመሆን ለሚፈልግ የሚጠቅም ኢንፎርሜሽን፣ ደንበኛ ወይም ደንበኛ ለመሆን ኢንፎርሜሽኑን የሚፈልግ ሰው በስልክ ወይም በኢንተርኔት አማካይነት በሚጠይቅ ጊዜ የሚሰጥበት ወይም በራስ አነሳሽነት የሚላክበት አገልግሎት ነው፡፡

3. "ኮርፖሬሽን" ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ብቸኛ የሆነው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ተብሎ ትርጓሜ የተሰጠው አካል ነው::

4. «ባለፈቃድ» ማለት የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን ለመስጠት ፈቃድ ያለው ሰው ነው::

5. «የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ» ማለት የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት ፈቃድ ወይም የኮል ሴንተር አገልግሎት ፈቃድ ማለት ነው::

6. «የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት (ቪ-ኢንተርኔት)» ማለት የኮርፖሬሽኑን የኢንተርኔት ባንድዊድዝ ወይም የኮርፖሬሽኑን የኢንተርኔት ኔትወርክ መሣሪያ ሊዝ በማድረግ ለተጠቃሚዎች የዳያልአፕ ኢንተርኔት አክሰስ አገልግሎት፣የዌብ ሆስቲንግ አገልግሎት፣የኢ-ሜይል እና ሌሎች ተመሣሣይ አገልግሎቶችን የመስጠት አገልግሎት ነው::

# አንቀፅ ሶስት
# ስለፈቃድ አስፈላጊነትና የፈቃድ አይነቶች

## 1. ስለፈቃድ አስፈላጊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት ወይም የኮል ሴንተር አገልግሎት ለማቋቋም የሚፈልግ ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከኤጀንሲው ፈቃድ ማውጣት አለበት::

## 2. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች

የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች

ሀ. የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት

ለ. የኮል ሴንተር አገልግሎት

ናቸው::

# አንቀፅ አራት
# ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ለተዘረዘሩት የፈቃድ አይነቶች ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሁሉም የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ አሰጣጥ  ላይ ተፈፃሚ የሆኑ የብቃት ሁኔታዎችን ማሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለእያንዳንዱ የፈቃድ አይነት ደግሞ ከዚህ የሚከተሉትን የብቃት ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡፡

**ሀ. ቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት**

የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት ፈቃድ ጠያቂ ቢያንስ

i. ሁለት በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ በኤሌክትሪካል ወይም ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች፣

ii. አንድ ከታወቀ የትምህርት ተቋም በኤሌክትሪካል፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በተመሳሳይ ሙያ ዲፕሎማ ያለው ቴክኒሽያን እና

iii. ኢንተግሬትድ ወይም ለየብቻቸው የሆኑ አንድ ራውተርና አንድ ለዳይል አፕ አገልግሎት ብቻ የሚውል አክሰስ ሰርቨር መሣሪያዎች

እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

**ለ. የኮል ሴንተር አገልግሎት**

የኮል ሴንተር አገልግሎት ፈቃድ ጠያቂ ቢያንስ፣

i. ሁለት በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ በኤሌክትሪካል ወይም ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች፣

ii. አውቶማቲክ የጥሪ ማከፋፈያ /አውቶማቲክ ኮል ዲስትሪቢዩሽን/ መሣሪያ እና

iii. ሁለት የጥሪ አስተናጋጅ ሰራተኞች (ኮል ኤጀንትስ)

እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. ባለሞያን ለተለያዩ የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃዶች ስለመጠቀም

የኮል ሴንተር አገልግሎት እና የቨርችዋል ኢንተርኔት አገልግሎት ፈቃድ ለማውጣት የሚፈልግ አመልካች በአንቀፅ አራት ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) (i) እና (ii) ሥር የተጠቀሱትን ባለሙያዎች በመጠቀም ሁለቱንም ፈቃዶች ለማውጣት ይችላል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ ሰው፡-

ሀ. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ከሚመለከተው መስሪያ ቤት የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

ለ. የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩን መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ. ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም የኢትዮጵያዊ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ የውጭ ዜጋ ከሆነ ይህንኑ ካርድ፣

መ. የባለሙያዎቹን የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እና ባለሙያዎቹ ተቀጣሪ ከሆኑ ከድርጅቱ ባለቤት ወይም ንግድ ድርጅት ጋር ያደረጉት የሥራ ውል

ማቅረብ አለበት፡፡

# አንቀፅ አምስት
# በኮርፖሬሽኑና ባለፈቃዱ መካከል የአገልግሎት አሰጣጥንና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ እና ጥራት መወሰንን በተመለከተ ስለሚደረግ ውል

1. የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ጥራት የሚወስን ውል በኮርፖሬሽኑ እና በባለፈቃዱ መካከል መፈፀም አለበት፡፡

2. የአገልግሎት  አሰጣጥ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ጥራት የሚወስኑት ውሎች በአንድ ዶክመንት ወይም በተናጠል ሊዘጋጁና ሊፈረሙ ይችላሉ፡፡

3. የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ጥራት ውል

ሀ. የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና ጥራት ውል ቢያንስ፡-

i. ኮርፖሬሽኑ ለባለፈቃዱ የሚሰጠውን አገልግሎት አይነትና አገልግሎቱን የሚሰጥበትን ጥራት ደረጃ ጉዳዮችን፣

ii. ለባለፈቃዱ በተዘረጋለት መሥመር ወይም በተሰጠው አገልግሎት ላይ ብልሽት በሚያጋጥም ጊዜ ቅድሚያ ሰጥቶ በአስቸኳይ ጥገና ስለማድረግ እና መሥመሩ ወይም አገልግሎቱ ለሥራ ዝግጁ ስለሚደረግበት ሁኔታ እና የጊዜ ገደብ እና

iii. በኮርፖሬሽኑ ጥፋት ባለፈቃዱ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ስለመካስ የሚመለከቱ ጉዳዮችን

መያዝ አለበት፡፡

4. የአገልግሎት አሰጣጥ ውል

ሀ. የአገልግሎት አሰጣጥ ውል ቢያንስ፡-

i. ኮርፖሬሽኑ ለባለፈቃዱ የሚሰጠው አገልግሎት አይነት፣

ii. ባለፈቃዱ ከኮርፖሬሽኑ ለሚያገኘው አገልግሎት የሚከፍለውን የአገልግሎት ክፍያና

iii. ውል ሊሰረዝ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች

መያዝ አለበት፡፡

ለ. ባለፈቃዱ ከኮርፖሬሽኑ ለሚያገኘው አገልግሎት ክፍያ መፈፀሙን ለማረጋገጥ በአገልግሎት አሰጣጥ ውል ውስጥ የዋስትና ሁኔታ ሊጨመር ይችላል፡፡

5. የአገልግሎት አሰጣጥ ውሉ በኮርፖሬሽኑ በኩል ሊሰረዝ የሚችለው ኤጀንሲው የባለፈቃዱን ፈቃድ ከሰረዘ፣ ባለፈቃዱ ለኮርፖሬሽኑ ለመክፈል የገባውን ክፍያ ግዴታ በአገልግሎት አሰጣጥ ውል ውስጥ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ፣ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሚያገናኘውን ወይም በጋራ የሚጠቀምበትን መሣሪያ ሲገለገል ኮርፖሬሽኑ ስለደህንነት ያወጣቸውን መመሪያዎች በግልፅ ሁኔታ ከጣሰ፣ ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ካጋጠመ ብቻ ነው፡፡

# አንቀፅ ስድስት
# የፈቃድ ማመልከቻ፣ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመከልከል

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት፡፡

2. አመልካቹ ላመለከተበት ፈቃድ ዓይነት በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን የብቃት ሁኔታዎች በሙሉ አሟልቶ ሲያቀርብ ኤጀንሲው ፈቃዱን ከአራት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

3. አመልካቹ ለጠየቀው የፈቃድ አይነት በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን የብቃት ሁኔታዎች በሙሉ ካላሟላ ኤጀንሲው ፈቃዱን ይከለክለዋል፡፡ ኤጀንሲው ፈቃዱን የከለከለበትን ምክንያት ከአራት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ መግለፅ አለበት፡፡

# አንቀፅ ሰባት
# ስለፈቃድ ጊዜ፣ ክፍያና እድሳት እንዲሁም ስለአገልግሎት ክፍያዎች

1. **ስለፈቃድ ጊዜና እድሳት**

ኤጀንሲው በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ የሚያገለግለው በተሰጠበት ጊዜ ላለው አንድ የመንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን በየዓመቱ እስከ የካቲት 30 ድረስ ባሉት ቀናት መታደስ ይኖርበታል፡፡

2. **የፈቃድ እና የእድሳት ክፍያ**

ሀ. የቨርቸዋል ኢንተርኔት አገልግሎት ፈቃድ ሲወሰድ ብር 533 (አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት) እና ፈቃዱ ሲታደስ ብር 166 (አንድ መቶ ስልሳ ስድስት) ለኤጀንሲው መከፈል አለበት፡፡

ለ. የኮል ሴንተር አገልግሎት ፈቃድ ሲወሰድ ብር 349 (ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ) እና ፈቃዱ ሲታደስ ብር 122 (አንድ መቶ ሀያ ሁለት) ለኤጀንሲው መከፈል አለበት፡፡

3. **የአገልግሎት ክፍያዎች**

ሀ. ኮርፖሬሽኑ ለሚሰጠው አገልግሎት ባለፈቃዶችን የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ አገልግሎቱን በስፋት ለማቅረብ የሚያበረታታ፣ ወጥነት ያለውና ለቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጪ ተብሎ የተተመነ ዋጋን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ኮርፖሬሽኑ የሚያስከፍለውን የአገልግሎት ክፍያ መተመንና ግልፅ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ. ኮርፖሬሽኑ የሚያስከፍለው የአገልግሎት ዋጋ ሲለወጥ የዋጋው ለውጥ ተግባራዊ ከሚደረግበት ከ30 /ሰላሳ/ ቀናት በፊት ለባለፈቃዱ በፅሁፍ እና ለሕዝብ ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን መግለፅ አለበት፡፡

# አንቀፅ ስምንት
# የባለፈቃዱ ግዴታዎች

1. ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያና አግባብነት ያላቸውን ሕጎችና ድንጋጌዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

2. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ በተሰጠው ፈቃድ መሠረት መስራት የሚችለው በፈቃዱ ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ብቻ ነው፡፡

3. ባለፈቃዱ ፈቃዱን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ማሳደስ አለበት፡፡

4. ባለፈቃዱ የሚጠቀምባቸው የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ከኤጀንሲው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው።

5. ባለፈቃዱ የሚጠቀምባቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን ፈቃድ ለተሰጠው አገልግሎት ብቻ ማዋል አለበት።

6. ባለፈቃዱ የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ ከወሰደ በኋላ ከኮርፖሬሽኑ ጋር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሠረት የውል ስምምነት መፈፀም አለበት።

7. ባለፈቃዱ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የአገልግሎት አሰጣጥ ውል ከመፈራረሙ በፊት አገልግሎት የሚሰጥበትን የኔትወርክ ዲዛይን ለኮርፖሬሽኑ ማቅረብ አለበት።

8. ባለፈቃዱ ከደንበኞች ጋር የአገልግሎት ውል መፈፀም አለበት።

9. ባለፈቃዱ የኮርፖሬሽኑን የንግድ ሥም ወይም ምልክት ለመጠቀም አይችልም።

10. ባለፈቃዱ ከኮርፖሬሽኑ ኔትወርክ ጋር የሚያገናኛቸውን ወይም በጋራ የሚጠቀምባቸውን ማናቸውንም መሣሪያዎች ኮርፖሬሽኑ ስለ ደኅንነትና ከአደጋ መከላከል ጋር በተያያዘ ያወጣቸውን መመሪያዎች የተከተሉ መሆን አለባቸው።

11. ባለፈቃዱ ማናቸውንም የኢንተርኔት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን ማዞሪያ አገልግሎቶችን መውሰድና መጠቀም ያለበት ከኮርፖሬሽኑ ብቻ ነው።

12. ባለፈቃዱ የማንኛውንም ሰው በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶችን ያለመደፈር መብት የማክበር ግዴታ አለበት።

13. የቨርችዋል ኢንተርኔት ባለፈቃድ ኮርፖሬሽኑ ወይም በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል በስራ ላይ ባዋለው የዶሜይን ስም አሰጣጥ ስርዐት መሠረት የዶሜይን ስም መውሰድ አለበት።

14. የኮልሴንተር አገልግሎት ባለፈቃዶችን መሣሪያዎች እርስ በእርሳቸው ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ባለፈቃዶች መሣሪያዎች ጋር ማገናኘት አይቻልም።

## አንቀፅ ዘጠኝ
## የኮርፖሬሽኑ ግዴታዎች

1. ኮርፖሬሽኑ በተመሳሳይ ደረጃ ውስጥ በሚገኙ ባለፈቃዶች መካከል ያልተገባ ልዩነት አያደርግም።

# አንቀፅ አሥራ አንድ
# ስለተጠያቂነት

1. l pEî L å}Šîb¿ †”³ e¼Y 49/1989 /ˆ¿ª paaE’å/ †¿dÎ 25 LPTr ¼× r £ÔÐL ሰው l’¿¯Eå ¨º£gG::

# አንቀፅ አስራ ሁለት
# ፈቃድ ስለመሰረዝ

1. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንቀፅ 8 ወይም በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተጠቀሱትን ግዴታዎች ካላከበረ፣ ወይም ፈቃዱን ያገኘው በሀሰት ወይም በተጭበረበረ መረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ወይም ከከሰረ ወይም ስራውን ከተወ፣ ወይም ከኮርፖሬሽኑ ጋር የፈረመው የአገልግሎት አሰጣጥ ውል በዚህ መመሪያ መሠረት ከተሰረዘ፣ ወይም Ôቃዱ መታደስ ያለበት ጊዜ ካለቀ Ôቃዱ ይሰረዛል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለፈቃድ ከኮርፖሬሽኑ ያገኘው አገልግሎት እንዲቋረጥ ይደረጋል።

# አንቀፅ አስራ ሶስት
# መመሪያውን ስለማሻሻል

የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ የማሻሻል ወይም የመለወጥ ሥልጣን አለው።

# አንቀፅ አስራ አራት
# መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 10 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 2 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ካሡ ይላላ (ዶ/ር)**

**የመሠረተ ልማት ሚኒስትር**